በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከኦገስት 11-20 እና ከኦገስት 21-31 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ..... - 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች- 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት..... - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... - 4 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... - 5 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... - 6 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ..... - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ..... - 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን..... - 8 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ..... - 8 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31፣ 2024..... - 9 -

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ..... - 9 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 9 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 10 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በጋምቤላ፣ በምዕራብ እና መካከለኛ ኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በምስራቅ እና ምዕራብ አማራ፣ በትግራይ ክልል፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በሲዳማ ክልል፣ በአፋር ክልል እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በባህርዳር 41.5፣ በመቀሌ 44.4፣ በአልጌ 70.0፣ በአርጆ 40.6፣ በአሶሳ 45.5፣ በአፅቢ 52.5፣ በጨፋ 75.6፣ በጭፍራ 84.4፣ በላይበር 76.0፣ በአምደወርቅ 42.2፣ 52.0፣ በቡሬ 40.0፣ በቻግኒ 43.8፣ በደብረ ወርቅ 48.9፣ በኢጃጂ 66.2፣ በፉኚዶ 68.0፣ በጊምቢ 45.1፣ በመተማ 52.0፣ በማጀቴ 79.4፣ በሞጣ 61.1፣ በኑራኤራ 67.8፣ በአዳማ 43.6፣ በሳውላ 44.2፣ በስርንቃ 55.1፣ በቴፒ 84.4 እንዲሁም በጉብሬ 54.1 ሚ.ሜ. የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፈው የኦገስት የመጀመሪያው አስር ቀናት በ57 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 60-84.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከበድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል ላይበር፣ ኢጃጂ፣ ፉኚዶ፣ ማጀቴ፣ ሞጣ፣ ኑራኤራ፣ አልጌ፣ ጨፋ፣ ጭፍራ እና ቴፒ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል:nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





**ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች**


ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአፋር ክልል ቂልበቱ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ እና ፋፋን ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋግህምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ መተከል፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ባስኬቶ፣ ጋሞ እና ወላይታ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ሸካ እና ኮንታ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከ101-270 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ8-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ባሌ ዞን፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኣሌ፣ ደቡብ ኦሞ እና ኮንሶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ቅልበቲ ዞን፤ ከደቡበ ምዕራብ ኢትዮጵያ

ክልል ምዕራብ ኦሞ ዞን ላይ ከ15-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-7 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ እና ቄለም ወለጋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማኦኮሞ ልዩ ዞን፣ ካማሺ፣ አሶሳ እና መተከል ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፣ ከሱማል ክልል ሲቲ እና ፋፋን ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ኮንሶ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ጋሞ፣ ባስኬቶ እና ደራሼ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ
የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠን ሆነ በስርጭት የተስፋፋና ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለተለያዩ ቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የክረምት ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ የመኸር ሰብሎች እድገታቸውን በተሟላ ሁኔታ ለማከናወን ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል የተገኘው እርጥበት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡

በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው ዝናብ ጋር ተያይዞ የጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡

በተለይም በከፋ ዞን በጠሎ ወረዳ፣ በድሬዳዋ ከተማ ዋሂል ወረዳ፣ በትግራይ ማእከላዊ ዞን አድዋ ወረዳ፣ በሸበሌ ዞን ሙስታሂል ወረዳ፣ በወላይታ ዞን ካኦ ኮይሻና ክንደ ኮደሻ ወረዳ ከፍተኛና ተከከታታይነት ካለው ዝናብ ጋር ተያይዞ በሰው ህይወት፣ በንብረት፣ በእንስሳት እና በሰብሎች ላይ ጉዳት እንደደረሰ ከተለያዩ የመስክ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል (ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፍት ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም የላይኛው እና የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ እና መካከለኛው ገናሌ ዳዋ እንዲሁም በታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የነበረው የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የከርሰ ምድርንም ሆነ የገፀ ምድር የውሃ ሃብትን በማጎልበት ወደ ግድቦች እና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን በመጨመር እንዲሁም የተለያዩ ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ ምንጮችን በማጎልበት ረገድ የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡

በሌላ በኩል ከነበረው ከፍተኛ እና ተደጋጋሚ የሆነ እርጥበት ጋር ተያይዞ በአባይ ተፋሰስ ፎገራ ዙሪያ እና በባሮ አኮቦ ተፋሰስ አኙዋክ ዞን ፑቻላ እንዲሁም በማጃንግ ዞን ሜጤ ወረዳ በጥቂት ተፋሰሶች ላይ የጎርፍ ክስተቶች ተስተውለዋል (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛ አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ የሚጠናከሩበት ጊዜ ነው፡፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆን፤ በየጣልቃው የሚኖረው ፀሐይ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ ቁልል ደመና፣ በረዶ፣ ነጎድጓድ፣ መብረቅና ከባድ ዝናብ እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በመሆኑም በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅና እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ የሚያስከትል ከባድ ዝናብ እንደሚኖር አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ ፡፡


በአጠቃላይ በመጪዎቹ አሥር ቀናት በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የወቅቱ ዝናብ ይቀጥላል፡፡ ስለሆነም ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግህምራ፣ አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፤ ማዕከላዊ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዌ፤ አሶሳ፤ ካማሺ ዞኖች እና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣ አኝዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ዞኖች፣ ጠምባሮ፣ ቀቤና እና ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድኦ፣ ባስኬቶ እና አማሮ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ምስራቅ ኦሮሚያ፣ ሰሜን ሶማሌ መደበኛው ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በሌላ በኩል አልፎ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አልፎ ከሚፈጠሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በደቡብ ኦሮሚያና የቡብ ምሥራቅ አከባቢዎች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

## እ.ኤ.አ ከኦግስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት በመጨረሻዉ አስራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡


በኦገስት የመጨረሻው ሳምንት የክረምት ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተመሳሳይ ጥንካሬ እንደሚቀጥሉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በፀሐይ ሀይል ታግዞ ከሚፈጠረው ጠንካራ የሆነ የደመና ክምችት ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶና



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ነጎድጓድ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8) ፡፡

Rainfall performance (mm) for 21-31 August 2024




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31፣ 2024
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት ለመኸር ሰብሎች ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በአንጻሩ በአንዳንድ ቦታዎች ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የውሃ በሰብል ላይ መተኛት፣ የመሬት አቀማመጣቸው



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ፣ እንዲሁም የሰብል በጎርፍ የመጠረግ ሁኔታዎች እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል እርጥበት በሚበዛባቸው አካባቢዎች የሰብል በሽታ መከሰት እና የአረም መስፋፋት ሁኔታዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ሰብሎች በጎርፍ እንዳይጠረጉ የጎርፍ መቀልበሻና ማፋሰሻ ቦዮችን ማዘጋጀት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ መስራት፤ የሰበል ማሳን በየጊዜው መከታተል፣ ለሰብል አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በግብርና ባለሙያዎች በመታገዝ በወቅቱ ርጭት የማድረግና እንዲሁም የፀረ-አረም እና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦገስት ሁለተኛ አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በአባይ፣ ተከዜ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው የገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች  ከመካከለኛ እስከ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለገጸ ምድር እና ለከርሰ ምድር የውሃ ሀብት መጎልበት አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ወደ ግዶቦች የሚገባው ውሃ ከፍተኛ በመሆኑ በቀጣይ አስር ቀናትም አሁናዊ የውሃ ከፍታቸው አስጊ በሆነባቸው እንደ ፊንጫዋ፣ ጣና በለስ፣ ከሰም እና ርብ የመሳሰሉት የሀይል ማመንጫ እና የመስኖ ግድቦች የቅርብ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ የአፈሩ እርጥበት ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ  የውሃ ስርገት ስለሚቀንስ እና የዝናቡ መጠን ከትንቱ የበለጠ ስለሚሆን ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተት እና የወንዞች ሙላት ሊከሰት ስለሚችል ማህበረሰቡና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et